# የኢትዮጵያ ልደት! ሁለት ሺህ
# ወይስ
# ሁለት መቶ ዓመት?

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት
(ኢዴኃሕ) የድጋፍ ኮሚቴ
በሎስ አንጀለስ

መስከረም 1ቀን 2000 ዓ.ም

# የኢትዮጵያ ልደት! ሁለት ሺህ
# ወይስ
# ሁለት መቶ ዓመት?!

የፊታችን መስከረም አንድ ካለፉት የዘመን መለወጫዎች ሁሉ የተለየ የሚሆነው ለምንድን ነው?

በመጭው መስከረም አንድ የአገራችን/ የኢትዮጵያ ዕድሜ ሁለት ሺህ ዓመት ስለሚሆን ነው:: ይህ ከክርስቶስ ልደት ጀምሮ ያለው ዕድሜዋ ብቻ ነው:: ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው ታሪኳ ሲደመርና ሲጨመር ዕድሜዋ ከሦስት ሺህ ዓመት እጅግ የላቀ ነው!!

በመሆኑም እጅግ ጥንታዊት ከሆነችው ኢትዮጵያ ጋር ሲነፃፀሩና ሲወዳደሩ፣ አብዛኞቹ በዛሬ ዘመን የሚገኙ አገሮች ገና በመዳ ሂደት ላይ ያሉ ታዳጊ ሕፃናት ናቸው ቢባል ታሪካዊ ሐቅን መግለጥና መጥቀስ እንጂ እነዚህን አገሮች መስደብና ማዋደቅ አይሆንም::

የኢትዮጵየ ታሪካዊ ጓደኞችና እኩያዎች እነባቢሎን፣ ጥንታዊትዋ/ የፈረኦኖች ግብፅ፣ ጥንታዊትዋ ግሪክ፣ ፋርስ፣ ቻይና፣ ሕንድና የመሳሰሉት ብቻ ናቸው::

ይህ መላው ዓለም የሚያውቀውና ሊካድ የማይችል ሐቅ ነው::

ይህንኑ ሐቅ በቅናትና በጠላትነት ተነሳስተው ሊያፈርሱት / ሊደመስሱት፣ ሊክዱት፣ ሊቀብሩት፣ሊደልዙት፣ሊሰርዙት የፈለጉና የታገሉ ሁሉ ሳይሳካለቸው ቀርቷል::

ይሁን እንጂ ይህ ዓይነቱ ሙከራ እስከ ዛሬም ቢሆን አልተቋረጠም:: አሁንም እንደቀጠለ ነው::

ይህንኑ ለመገንዘብና ለማረጋገጥ የወያኔ ታሪክ ጸሐፊዎችን መስማት ብቻ በቂ ነው:: እንደ ወያኔ ታሪክ ጸሐፊዎች ከሆነ የኢትዮጵያ ልደትና ሕልውና ዕውን የሆነው ከትናንቱ ከጳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ነው!!

የወያኔ የታሪክ ፋብሪካ አምርቶ የተፋውን ተቀብለን ያገራችንን ዕድሜ ስንተምን፣ ኢትዮጵያ እንኳን ሁለት ሺህ ዓመት ሊሆናት ገና ሁለት መቶ ዓመትም አይሞላት!!

በተጨማሪም ወያኔዎች፣ ይህች የመቶ ዓመትዋ ኢትዮጵያ ከትግራይ ሕዝብና ታሪክ ጋር አንዳችም ዝምድና እና ትስስር እንደሌላት ሲሰብኩና ሲያውጁ ሰንበተዋል፣ በወያኔ ታሪክ ጸሐፊዎች አተረጓጎምና አነጋገር:-
- ትግራይ የመቶ ዓመትዋ ኢትዮጵያ ( የ"ዐባይ ኢትዮጵያ ") አባልም አካልም አይደለችም/ አልነበረችም::
- በመሆኑም የትግራዊያን አገር ትግራይ ብቻ ነች:: ትግራዊያን "የዐባይ ኢትዮጵያ ጉዳይ" (ከትግራይ ውጪ የሆነ ኢትዮጵያ ጉዳይ) አያገባቸውም/ አይመለከታቸውም::

ስለሆነም ከትግራይ ውጭ ለሆነው " የዐባይ ኢትዮጵያ" ሕዝብ " የአክሱም ሐውልት ምኑ ነው?" :: የዐባይ ኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን የታሪክ ቅርስ ከትግራዊያን ጋር የሚጋራበት ምክንያትም/ መብትም የለውም:: የምን ከፍ ከፍ/ የምን ጢጋ ጢጋ ነው?!
- የአክሱም ሐውልት እና ቅርስ ብቸኛው ባለቤት "ወርቅማው" የትግራይ ሕዝብ ነው!!
- " ወርቅና አፈር መች ተቀላቅሎ?"
- " የዐባይ ኢትዮጵያ" አባልና አካል አይደለንም በማለት ብቻ አላቆሙም::
- በኢትዮጵያ ቅኝ ገዢነት የተያዝን "አረቦች ነን" አሉ::

- ከኢትዮጵያ ጋር ተዋግተን ነፃ "የአረብ" (የትግራይ) ሪፑብሊክ እንመሰርታለን ብለው በነጋዳፊ በኩል ለመላው የአረብ ዓለም ግባቸውን አውጀው አስታወቁ::

በዚህም እምነታቸውና አቋማቸው ምክንያት፤ በሕዝቦችዋ እኩልነትና ወንድማማችነት ለምትመሰረት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ለመታገል ትግራይን ደጀንና ማፈግፈጊያ በማድረግ ተሰልፎ የነበረውን ኢህአሠ (የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ሠራዊት) "አገራችሁን ሂዱና ነፃ አውጡ ፤ ትግራይ አገራችሁ አይደለችም:: እናንተ የዐባይ ኢትዮጵያ ቡድኖች ናችሁ:: እኛ አረቦች ነን፤ ታግለን ከኢትዮጵያ ነፃ እንወጣለን:: ለማረጋገጥ እናንተ የዐባይ ኢትዮጵያ ተቆርቋሪዎች (የትግራይ ጠላቶች) ናችሁ በማለት ከአንድ ወንድማማች ሕዝብ ቀርቶ ከለየለት ወራሪ አረመኔ ፋሽስት በማይጠበቅ ሁኔታ የኢህአፓን ታጋዮች ጨፍጭፈው ከትግራይ አባርረዋል::
- ሕብረ-ብሔራዊ ሆነው ለአንድነትና ለእኩለነት መቆማቸውና መታገላቸው ነው የወያኔ መራራ ጠላት ያደረጋቸው!!
- ትግራይን " በቅኝ ግዛትነት" ለያዘው ለዐባይ ኢትዮጵያ ዕድገትና አንድነት መቆማቸው ነው!
- ለዚህም ነው "ለትግራይ ያልሆነች ኢትዮጵያ ( ለትግራይ ብቻ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትፍረስ/ ትደርመስ" ብለው እምነታቸውንና ግባቸውን ጮኸውና ተጣርተው በአዋጅ ያሳወቁት::
- ይህን አምነውና ይህን ብለው ነበር የተነሱት:: የትግራይ ነፃ አውጪ ተዋጊዎችና መሪዎች:: ወያኔዎች::
- የትናንቶቹ የመቶ ዓመት ታሪከኞች/ የትናንቶቹ ትግራይ የዐባይ ኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ተደርጋለች ሲሉ የነበሩት ወያኔዎች ናቸው::

ዛሬ የኢትዮጵያን የሁለት ሺህ ምዕተ-ዓመት ዘካሪ እና አጋፋሪ ሆነው እንደልማዳቸው ነጋሪት እየጐሰሙና ከበሮ እየመቱ ጉሮሮአቸው እስኪተረተር የሚጮሁትና የሚያጓሩት!!

ከአድዋና ከትግራይ አርቀው ማየት ከማይችሉ ጭንቅላቶች ፈልቆና ፈስሶ ከደደቢት የታሪክ ፋብሪካ የተመረተው የኢትዮጵያ ሁለት መቶ ዓመት ታሪክ በጠብመንጃ ኃይል በአዋጅ ሲነገር ሲከበር ሰንብቷል:: ዛሬ ደግሞ አነዚያው ታሪከኞች/ ወያኔዎች ከተወርዋሪ ኮከብ ፈጥነው ከ200 ዓመት ወደ ሁለት ሺህ ዓመት ዘልለው ተሻግረዋል!!

በወያኔ ቤት የመዝለል፤ የመገለባበጥና እንደ እስስት የመለዋወጥ ችግር የለም:: በእውነትና በሐሰት (Truth and false hood በፈጠራና በሁነት fact and fiction) መካከል ድንበር የለም!!

ወያኔ የራሱ የሆነ፤ ከሌላ ከማንም ጋር የማይጋራው የውነትና የውሸት መስፈርት አለው:: እውነትና ሐሰት ይቀያየራሉ:: ይፈራረቃሉ:: በወያኔ ፍላጎትና ፈቃድ!! ሰሪ/በባሪያቸው፤ ፈጣሪ/ቀባሪያቸው ወያኔ ብቻ ነው::

በአንድ ሰሞን የማምንበትና የቆረብኩለት፤ ነፍሴና ሥጋዬ እስኪሰነባበቱ ድረስ የምታገልለት አቋሜና መስመሬ ነው ብሎ ያወጀውን በአንጻፍታ አሽቀንጥሮ ከመሬት ላይ ይጥለዋል::

ጥንብ ርኩሱን ያወጣዋል:: ሲያወግዘውና ሲያዋድቀው የቆየውን ደግሞ በድንገት አንስቶ ያቅፈዋል:: ጥሎ እስኪያፈረጠው ድረስ አዝሎ ከጀርባው ላይ እሽሩሩ ይለዋል::

በወያኔ ቤት ያስታወኩትን መብላት፣ ገድሎ ማልቀስ፣ ሰውሮ መፈለግ አስነዋሪም አሳፋሪም ሆኖ አያውቅም::

የኢትዮጵያን ዕድሜ አስመልክቶ ወያኔ የሚያሳየው ትያትርና አክሮባት የመሠረታዊና የዘወትር ባሕርዩ አካልና ነፀብራቅ ነው እንጅ በድንገትና በስህተት ላንዴና በአንድ ወቅት ብቻ የተከሰተ ነገር አይደለም::

ወያኔ የኢትዮጵያን ዕድሜ አስር(10) ጊዜ ያሳነሰው ሆን ብሎ እንጂ ተሳስቶ አይደለም ለማለት ነው::

የወያኔ አቋምና ባሕርይ በየጊዜው ይለዋወጣል:: በእየዕለቱ ÷በየሳምንቱ÷ በየወሩና በየዓመቱ አዳዲሰ መስመርና አዋጅ የሚያመርቱ ፋብሪካዎች አሉት:: አዳዲስ ቀለም እየተቀቡ የሚያሰለቹ እጅ እጅ የሚሉና የሚጐመዝዙ አሮጌ ውሸቶች እየተደጋገሙና እየተፈራረቁ በወያኔ ብቸኛ ትአዛዝና ቁጥጥር ስር በሚተዳደሩ ጋዜጦች፣ ራዶዮኖች፣እና ቴሌቪዥኖች ይሰራጫሉ::

ስለዚህ ወያኔ የኢትዮጵያን " የሁለት መቶ ዓመት" ልደትና ታሪክ ጥሎና ሰርዞ የሁለት ሺህ ዓመት ልደትዋ አክባሪና ዘካሪ ለመሆን የበቃው በምን ተአምር ነው? ለሚለው ጥያቄ አሳማኝ መልስ ማግኘት የምንችለው <u>እንዲያው በቀላሉና በደፈናው ወያኔ የውሸት ጐተራ ነው፣ ውሸት ማውራት ልማዱ ነው፣ ምላሱ ውሸት ማኘኰድኰድ አእምሮው ውሸት መፈልፈልና መቀፍቀፍ ብቻ ነው የሚችለው</u>:: ስለዚህ ተፈጥሮውን ተገንዝበን እንዘንለት:: እርሱም እኮ ቢሆን " ኢትዮጵያዊ" ነው! የሚል ሊሆን አይችልም:: ከላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ መልስ የሚሆነው::

አሳማኝ መልስ ላይ ለመድረስ መነሳት ያለበት ጥየቄ በየጊዜው የውጭ ገፅታዎቹ ሲፈራረቁ፣ ሲለዋወጡና ሲገዳደፉ፣ ሳይቀየርና ሳይቋረጥ፣ ተከታተትሎና ተቀጣጥሎ ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ( እስከዛሬ ) ድረስ የወያኔ ባሕርይ ተፈልጎ ሊገኝ ይችላልን? ከአለና ከተገኘስ የትኛው ነው? በሌላ አገላለፅ ወያኔ የሚመራበት መሰረታዊና ቀዋሚ የፖለቲካ ርዕዮት አለውን? የወያኔ መነሻና መድረሻ ከየት ወዴት ነው?

ወያኔ ከትግራይ ውጭ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብና ምድር የባዕድ አገርና ጠላት እንጂ የራሱ አገርና ወገን አድርጎ እንደማያየው ከላይ ተጠቅሷል:: ትግራይ የዚሁ የባዕድ አገር ቅኝ ተገዢ ሆና እንደነበረች ወያኔ በተጨማሪ ቃሉን ሰጥቶ እንደነበር የሚታወስ ነው:: በመሆኑም አገሩን ነፃ ማውጣትና ለትግራይ ጥቅምና ደህንነት ብቻ መታገል የመጀመሪያና የመጨረሻ ግቡ ነበር(ነውም?) ማለት ነው:: ወደ ግቤ ያቀራርበኛል/ ያደርሰኛል ብሎ ያሰበውንና ያመነውን ሁሉ ከማድረግ ያመነታበትና የተቆጠበበተ ጊዜ የለም::

- ከተትረፈረፈው ያረብ ፔትሮ ዶላር ዘካ(ምፅዋዕት) ተቀብሎ ነፃ የምትወጣዋን የትግራይ ሪፑብሊክ ለማቋቋምና ለማጠናከር ፣ "ትግራዊያን አረቦች ናቸው" አለ ወያኔ ! በተናጠል ወይም በተጣማሪነት ከሻዕቢያ ጋር (ትግራይ/ትግርኝ) የትግራይ/"አረብ" ሪፑብሊክ ለመፍጠር ወጥነውና ቃጥተው ቢሆን ነው ትግራይን ከኢትዮጵያዊነት ወደ አረብነት "የለወጥዋት":: ትግሪዊያን አረቦች ከሆኑ የሚኖሩባት ምድር የአረብ አገር እንደምትሆን በግልፅ የሚታይ ነው!
- በዩናይትድ እስቴትስ መሪነትና አቀነባባሪነት፣ ከምዕራብ መንግሥቶችና ከአረብ አገሮች በተቀበሉት ትዕዛዝና ሁለንተናዊ ርዳታ፣ ሻዕቢያና ወያኔ ደርግን ለመገርሰስ ለተደረገው ትግል ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል::

- በተጨማሪም በእኩልነት ላይ ለምትመሰረት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ በመታገል ላይ የነበሩ ኃይሎች ደርግን መተካት እንዳይችሉ፤ ሻዕቢያና ወያኔ በተቀበሉት ትዕዛዝና መመሪያ መሠረት በተደጋጋሚ ወግተው አዳከመዋቸዋል፡፡
- ከደርግ ውድቀትና ሽንፈት በኋላ ሻዕቢያና ወያኔ፤ የአረብ/ትግራዮች ሪፑብሊክ (ሪፑብሊኮች) አቋቁመው ቀይ ባሕርን "የአረብ ባሕር" ለማድረግ የነበራቸው ምኞትና ውጥን ለእሥራኤል የማይዋጥለት ሆኖ ስለተገኘ ተቀልብሶ ይሆናል፡፡
- ከላይ በተጠቀሱት ኃይሎች ትዕዛዝና ፈቃድ፤ ሻዕቢያና ወያኔ ተልዕኮአቸውን አሟልተው ስላጠናቀቁ "ዐባይ ኢትዮጵያን" (የቀድሞ "ቅኝ ገዢአቸውን") በድል አድራጊነት ተረክበው ተቆጣጠሩ፡፡ እነዚህ የተገነጠሉና "ነፃ" የወጡ አገሮች በሻዕቢያና በወያኔ መሪነት ከትግርኛ ተናጋሪዎች ውጪ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ሕዝብና ምድር <u>በወራሪነትና በጠላትነት ይዘው ወደቅኝ ግዛትነት እና ቅኝ ተገዥነት ለወጡት፡፡</u>
- ጠላትነታቸውና ወራሪነታቸው በርቶ እንዳይታይ ሻዕቢያ ሽኚ ሆኖ (መስሎ) ወያኔ ደግሞ ራሱን "<u>የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር</u>" አሰኝቶ በጣምራነት የጠላታቸውን አገር ከመዳፋቸው ውስጥ አስገቡት፡
- ይጠቅመናል ብለው ያሰቡትን ሀብትና ንብረት ሁሉ ነቅለው/ነቃቅለው፤ አፍርሰው/አፍሰው፤ ጭነው/አግዘው ወደአገራቸው አሻገሩት፡፡ የማይፈልጉትንና ለማጋዝ የማይቻላቸውን ሁሉ በደማሚት እያፈረሱ፤በንብ እየወረወሩ አቀጣጥለው አመድ አደረጉት፡፡
- ለመጀመሪያ ሰባት ዓመታት ሻዕቢያና ወያኔ በጥምረት፤ ከተነጣጠሉ በኋላ ደግሞ ወያኔ በብቸኝነት የሰሩት ወንጀልና ግፍ ልክና መጠን ያለው አይደለም፡፡ ተወርቶ/ተዘርዝሮ የማያልቅ ተጠልቆ/ተቀድቶ የማይደርቅ ነው፡፡ የተሟላ ዘገባውን ለታሪክ ሙያተኞች ትተን ወደ ተነሳንበት ነጥብ መመለስ የግድ የሚል ነው፡፡

ይኸውም፡-

<u>አረብ ነኝ ሲል የቆየው ወያኔ፤ አገሩን "ነፃ" ካወጣ በኋላ ተመልሶ "ኢትዮጵያዊ"</u> ነኝ ብሎ ወደ መሐል አገር የወረደው ለምንድር ነው? የአረብ ፔትሮ ዶላር ዝቆ የትግራይ/ዓረብ ሪፑብሊክ አቋቁሞ የአረብ ሊግ አባል መሆን ስላልተቻለውና በትግራይ ምድር ተገድቦ የመኖር ምርጫ የማይሆንና የማይታሰብ ሆኖ ስላገኘው ይሆናል፡፡

ከትግራይ ውጭ ያለውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነትና ወንድማማችነት ፈልጎ እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ወያኔ አዲስ አበባን ከረገጠበት ወቅት ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ትግርኛ ተናጋሪ ባልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚፈጸመው ግፍና በደል ከመረረ ጠላት እንጂ ያንድ አገርና ሕዝብ አካልና ወገን ከሆነ ቡድንና ኃይል የሚጠበቅ አይደለም፡፡ ስለዚህ ወያኔ " የኢትዮጵያዊነት" ( "የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያው ግንባር") ጭንብል አጥልቆ ወደ መሐል አገር የወረደው ከትግራይ ውጪ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በጦር ኃይል አንቀጥቀጦና ደፍጥጦ ያገሪትዋን ንበረትና የሀብት ምንጭ ሁሉ ለመያዝና ለመቆጣጠር ነው፡፡ የትግራይን ምድር ለማልማትና በኢንዱስትሪ ለማበልፀግ ነው፡፡ የወያኔ "ኢትዮጵያዊ" መስሎ ወደ መሐል አገር መዝለቅ የስልት እንጂ የእምነትና የርዕዮት ለውጥ አይደለም፡፡

ወሳኝና መሠረታዊ የሆኑ <u>የደህንነት የመከላከያ</u>፤ የፖለቲካ ተቋሞች <u>አወቃቀር አሠራርና አመራር በወያኔና በትግርኛ ተናጋሪዎች የተያዘና የተመላ ነው</u>፡፡ የቀረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ያገለለ ስርዓትና አስተዳደር የጠላትና የቅኝ ገዢ ካልሆነ ሌላ ምን ሊሆን/ ምን ሊባል ይችላል?! በየቦታውና በየጊዜው " ኢትዮጵያን የመግዛት መብት ያለው ትግራዊ ብቻ ነው" ሲሉ እንደተደመጡ ናቸው፡፡ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በትግራይ ነገሥታትና አምባ ገነን ቡድኖች የመገዛት ግዴታ አለበተ ማለት ነው!?

ስለዚህ ትግርኛ ተናጋሪ ያልሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ አገሩ ተወርሮ፣ መብቱና ንብረቱ ተነጥቆና ተቀምቶ እየተበዘበዘ ስለሆነ ወያኔ ሁልጊዜም በጥርጣሬና በጠላትነት ዓይን እንደተመለከተውና እንደተከታተለው ነው:: በገፍ የሚገደለው፣ የሚታሰረውና የሚሰደደው የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የደቡብ ሕዝቦች......ወገን የሆነው ነው::

በጉዞ ላይ ሆኖ ወያኔ ራሱ ፈትሎ ራሱ ሸምኖ አዲስ አበባ ሲደርስ የተከናነበው ማደነጋገሪያ( "ኢህአዴግ") ሲገለጥ፣ በ"ኢትዮጵያ") ስም የተሸፈነ ያንድ ብሔረሰብ መንግሥት ብቻ መሆኑ በርቶና ደምቆ የሚታይ ሐቅ ነው::

"ኢህአድግ" ስለተባለ፣ ወያኔ ከተነሳበት ዓላማ አንድጋት እንኳን ወደኋላ አላለም:: ወያኔ የትግራይን ጥቅምና የበላይነት ብቻ የሚያስከብርና የሚያስቀድም ድርጅትና መንግሥት መሆኑ አልተቀየረም:: ኢትዮጵያን ወርሮና "ኢትዮጵያዊ" መስሎ የትግራይን ጥቅምና የበላይነት ለማስከበር ታልሞና ታስቦ የማይገኝ ዕድል ገጥሞታል! ስለሆነም "<u>ኢህአዴግነት</u>" እና "ኢትዮጵያዊነት" ለወያኔ የስልት እንጂ የዓላማና የእምነት ለውጥ አይደለም ለማለት ነው::

ዛሬ የኢትያጵያን የሁለት ሺህ ምዕተ-ዓመት ( millennium) በዓል ለማክበር የሚጣራውና የሚሯሯጠው ወያኔ አዲስ አበባ በገባበት ሰሞን <u>የኢትዮጵያ ታሪክ</u> ብሎ ሲሰብክና ሲያውጅ የነበረው ለምንድን ነው?

የኢትዮጵያን ታሪክና ዕድሜ ማስታወሰና ማወቅ ተስኖት ስለነበር አይደለም:: የኢትዮጵያን ታሪክና አንድነት ወደአንድ መቶ ዓመት ዝቅ ማድረግ የተመሰረተበትን ዓላማ ( የትግራይን የበላይነት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያመቸው ሆኖ ስላገኘው ነው:: የማረካቸውን የደርግ ወታደሮች፣ ከየመንገዱና ከየጥሻው ለቃቅሞ የሰበሰባቸውን ፍርፋሪ ለቃሚዎች፣ ሆዳሞችና መስሎ አዳሪዎች በየብሔረ-ሰባቸው አንድኖ አደራጃቸው:: በአምሳሉ ቀርፆ ፈጠራቸው::

<u>ልክ "እንደትግራይ" በኢትዮጵያ ለመቶ ዓመት ቅኝ ተገዝተው የነበሩ ብሔረ-ሰቦች ሁሉ በወያኔ ድል አድራጊነትና ተቆርቋሪነት "ነፃነታቸውን"</u> ተጐናጸፉ!!

- ይሁን እንጂ የወያኔ የክልል ፖሊሲ ለብ/ሰቦች የተሟላ የራስ ገዝነት ስልጣን አላስገኘላቸውም:: በእኩልነትና በወንድማማችነት ሊያስተሳስሩዋቸውና ሊያቀራርቧቸው የሚችሉ የኢኰኖሙ፣ የፖለቲካ፣ የባሕል...ወዘተ ማዕከሎችና ተቋሞች አልተዘረጉላቸውም:: በመሆኑም በነፃነትና በክልል ስም ብሔረ-ሰቦች እንዲራራቁ፣ እንዲተናነቁ፣ እንዲጋጩና እንዲናጩ ተደረጉ::
- ወያኔ ሆን ብሎ ኦነጎችንና ኦህዴዶችን አስተባብሮ በሐረር፣በአርሲ፣ በአሶሳ አፈር ገፊ አማሮችንና የሌላ ብ/ሰብ አባሎችን በሚዘገንንና ለወሬ በማይመች መልክ አስጨፈጨፈ:: የፈጸመውን ወንጀል መሳሪያ ካደረጋቸው በኋላ ወያኔ ኦነጎችን በጥፋተኛነት ከሰሰ!
- በነዚህ አካባቢዎች የተፈፀሙ ወንጀሎች በተለያዩ ክልሎችና ብ/ሰቦች መካከል ተበራክተው ተደጋገሙ::
- ከትግራይ ውጭ የሚኖረውና ወያኔ የወረረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ክንዱን አስተባብሮ በጠላቱ ላይ እንዳይነሳ በእርስ በእርስ ጥርጣሬና ፍራቻ ውስጥ ተዘፍቆ በየክልልና በተናጠል ለወያኔ ጥቃት ተዳረገ/ ተጋለጠ::
- በመሆኑም ወያኔ ለየብ/ሰቡ የሰጠውን "ነፃነት" ዋጋ ተቀበለ እያንዳንዱም ብ/ሰብ "የነፃነቱን ዋጋ" ተገድዶ ከፈለ! እየከፈለም ነው::
- የየብ/ሰቡ የወያኔ ድርጅቶች (የኢህአዲግ አባል ድርጅቶች) ነፍስ የሚዘሩትና የሚሞቱት በወያኔ ፍላጎትና ፈቃድ ስለሆነ ተጠሪነታቸው ለወያኔ (በወያኔ

ለሚመራው ማዕከላዊ/ፌደራል) መንግሥት እንጂ "ለሚወክሉት" ሕዝብ እንዳልሆነ ግልጥ ነው::

- በዚህም ምክንያት የየብ/ሰቡ የወያኔ ድርጅቶች በማዕከላዊ መንግሥት ስም ወያኔ ከየክልሉ የሚዘርፈውን ንብረት፤ የተፈጥሮ ሀብትና በጀት ማቀነባበርና ማቀላጠፍ እንጂ መከልከልና መከላከል አይችሉም:: አይፈልጉምም:: የየክልሉ የወያኔ ጉዳይ አስፈጻሚዎችና ተላላኪዎች ናቸውና::
- ወያኔ ትናንት የኢትዮጵያን ዕድሜ ወደ አንድ መቶ ዓመት ያወረደው፤ "በነፃነትና" በክልል ስም ብ/ሰቦችን አባልቶ፤የትግራይን ሁለንተናዊ የበላይነት ለማስፈንና የትግራይን ጥቅም ብቻ ለማስከበርና ለማስጠበቅ ነበር/ነውም::

ዘንድሮም ቢሆን ወያኔ የኢትዮጵያን ምዕተ-ዓመት የሚያከብርበት ምክንያት ከትናንቱ "የአንድ መቶ ዓመት" ታክቲክ የተለየ ግብና ሚና ያለው አይደለም::

ዛሬ ወያኔዎች የመላው ኢትዮጵያ ንብረትና መብት ብቸኛ ባለቤት እንደሆኑ ያደባባይ ምስጢር ነው:: መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነርሱን ሁለንተናዊ የበላይነት ተቀብሎ በአንድነት እንዲኖር ምኞታቸውና ፀሎታቸው ነው:: መብታቸውና ንብረታቸው ሳይቀናነስና ሳይሸራረፍ እንደተከረና እንደተጠበቀ እንዲቆይ ይመኛሉና:: የወያኔዎች ሁለንተናዊ የበላይነትና "የኢትዮጵያ" ሉዑላዊነት አንድ እየሆኑ መጥተዋልና! "የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ማለትና የወያኔ ሁለንተናዊ የበላይነት አንድ እየሆኑ መከሰትና መነገር የጀመሩት ገና ዛሬ አይደለም:: ሰንብቷል:: አንድ ምሳሌ መጥቀስና ማስታወስ ብቻ ይበቃል::

- ሻዕቢያና ወያኔ ኢትዮጵያን በኀብረት ወርረው ለሰባት ዓመት በተጣማሪነት ሲበዘብዟትና ሲገዘግዟት ከቆዩ በኋላ በንብረት ዝርፊያና ክፍያ ላይ ተጣሉ:: የሁለቱ ዘራፊዎችና መዝባሪዎች ጥል "የባድመ ድንበር" ግጭት ተደርጎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተነገረ:: "የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ተደፈረ" (ወያኔ በሻዕቢያ ተሸነፈ/ ተበለጠ!) ድንበር ተጣሰ አገር ተቆረሰ ብሎ ወያኔ እሪ አለ! ወያኔ ለአጋርነት ያሰለፋቸው 80 ሺህ ኢትዮጵያውያን ገሚሶቹ ፈንጂ ላይ ተራምደው ተበጣጠሱ:: የቀሩት ደግሞ በሻዕቢያ መድፍና መትረየስ ተቆልተው ረገፉ::
- ያ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ከተፈጀና ከተሰዋ በኋላ ተቆርሷል የተባለው መሬት ለሻዕቢያ እንዲመለስ ወያኔ ተስማምቶ ፈረመ:: ሻዕቢያን አግልሎና አባሮ፤ ወያኔ የኢትዮጵያ ሀብትና ንብረት ብቸኛ ባለቤት ሆነ:: ጥያቄ ውስጥ ገብቶ የነበረው "የኢትዮጵያ ሉአላዊነት" ተመለሰ/ ታደሰ!!! ወያኔ ብቻውን ነገሰ!!!
- ዛሬ ደግሞ "አሸባሪዎችን" ከሩቁ ለማቆምና ለመገደብ ( "የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማስጠበቅ") በሚል የቅጥፈት ሽፋን ወያኔ የሶማሌን ሕዝብ በአይሮፕላን፤ በታንክና በመትረየስ እየረሸነና እያቃጠለ ነው:: ይህ ሁሉ የሚያደርገው የጌቶቹ የኃያላን መንግሥቶች ሁለንተናዊ (የፖለቲካ/ የገንዘብ እርዳታ) እንዳይቋረጥበት ነው::
- የኢትዮጵያ ሕዝብ አንቅሮ ስለተፋው ተደግፎና ተንጠልጥሎ ያለው በባዕድ ኃይሎች እርዳታና ፍላጎት ብቻ ስለሆነ ነው:: ወያኔ ድጋፍና ገንዘብ የሚሸምተው ሁልቆ መሳፍርት የሌለውን የኢትዮጵያ ወጣትና ምስኪን ዘላን ሱማሌን በማጨራረስ ነው::

በአሁኑ ወቅት ደግሞ ወያኔ የኢትዮጵያን ሁለት ሺህ ምዕተ-ዓመት አድምቆ ለማክበር የተጣደፈበት ምክንያት ምንድን ነው?!

- ወያኔ በመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መተፋቱ ሁሉም የሚያውቀው ነው:: ተንጠላጥሎ የሚወዛወዘው በጠብመንጃ ኃይልና በባዕድ ጌቶቹ ዕርዳታ ላይ ብቻ ነው::
- ወያኔ በ97ቱ ምርጫ በመሸነፉ ምክንያት "ድምፄ ይከበር" ብሎ የተሰለፈውን ሰላማዊ ሕዝብ በአጋአዚ ጦር አስጨፍጭፏል::

- ይህ ወያኔ የወሰደው ዘግናኝ ርምጃ ራሱን ብቻ ሳይሆን " በዴሞክራሲያዊ ግንባታ ሂደት" ስም ሽፋፍኖው ሲደገፉት የቆዩት ጌቶቹንም ጭምር አጋልጧል:: በግንቦት 97ቱ ምርጫ ምክንያት ፤" ዴሞክራሲያዊ" መደበቂያው ተገፍፎ ፋሽስትነቱ ተራቁቶና ደምቆ በመላው ዓለም ፊት ተጋልጧል::
- የኢትዮጵያን የሁለት ሺህ ምዕተ-ዓመት በዓል አጻምቆ በማክበር የተራቆተ ክፉ ገላውን ለመሸፈን የሚያደርገው ጥረት ይመስላል::

እንደ ሚያዝያ 29/97 ዓ.ም ወያኔ ራሱ ዘፋኝ ራሱ ተቀባይ፤ አውራጅና አጨብጫቢ ሆኖ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደስታና ርካታ ለመላው ዓለም ለማሳየትና ለማሰማት የተመኘው የሕልም ሩጫ ይመስላል፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን፤ " ሚሊኒየም" ማለት " ምንም (ይህ ነው የሚባል ጥሩ ነገር) የለም" ብሎ ከደመደመ ቆይቷል!!

## በሚሊኒየሙ ዋዜማና ሰሞን የብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ ምን እየመሰለ ነው?

- ብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከ ዳር ( ከመቸውም ይበለጥ በከፋ መልክና መጠን) በረሃብ እየተጠበሰና እየረገፈ ነው፤
- የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከ$500 - $700 ደርሷል፤
- አንድ ፈረሱላ በርበሬ ከሺህ ($1000) ብር በላይ ያወጣል፤
- የማዳበሪያ ዋጋ ከፍሎ ለራሱና ለቤ/ሰቡ ልብስና ጉርስ ምንም የማይተርፈው ገበሬ እርሻውን ጥሎ /ቤተሰቡን በትኖ ወደ ከተማ መጉረፉ (ለልመና/ለጎዳና ኑሮ) እየጨመረና እየተበራከተ መጥቷል፤
- የመብል እህሎችና የስጋ ከብቶች (በግ፤ ፍየል፤ ዶሮ ሳይቀር) የወያኔ የንግድ ድርጅቶች በቀጥታ ከገበሬዎችና ከከብት ባለቤቶች በርካሽ እየገዙ ወደውጭ አገር ይልኩታል:: አገር ገበያ ውስጥ ለድህ የሚሆንና ለድሀ የሚቀር ነገር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያነሰ እየተቀነሰና እየተመናመነ ሄዷል፤ በአዲስ አበባና በየከተማው፤ የብዙሃኑን ምስኪን ጎጆ እያስፈረሱ በ$500. ዶላር የማመልከቻ ዋጋ ከውጭ ለሚገባው ባለገንዘብ መሬት እየመሩት ናቸው:: እንደአሁኑ ከቀጠለ የማገዶ እንጨት ችግር አይኖርም:: የድሀ ቤት ይፈርሳል፤ እንጨቱ ይቃጠላል፤ አመድ ይሆናል፤ ከቦታው ላይ የባለገንዘብ ቤት ይተካበታል/ ይሰራበታል::
- በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ፍርድ ቤት የመቅረብ ዕድል እንኳን ተነፍጓቸው አስታዋሽ አጥተው በእሥር እየማቀቁ ናቸው::
- የበዓሉን ድምቀት እንዳይቀንሱና እንዳያራክሱ ቁጥራቸው እስከ 180 ሺህ የሚደርስ ጐዳና አዳሪዎች እንደ ቆሻሻ ተለቅመውና ተዝቀው ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ በርቀት ተወርውረዋል::
- ከውጭ አገር ለሚመጡ ዘፋኞች ከሚሊዮን ዶላር በላይ ወጭ ተደርጓል ወዘተ.....

## የዛሬው የወያኔ ድግስ ምን ያስታውሰናል?

1. የወሎ ሕዝብ እንደ ቅጠል ሲረግፍ ለ80ኛው የአፄ ኃይለሥላሴ ልደት በዓል በብዙ መቶ ሺህ ብር ወጪ የተዘጋጀው ድግስ፤
2. ኢሠፓ አሥረኛ ዓመቱን ሲያከብር (በብዙ የኢትዮጵያ ክፍሎች ብዙሃኑ በረሀብ ሲወድም) በብዙ ሚሊዮን ዶላር የተሠራው የመሰብሰቢያ አዳራሽና የተዘጋጀው ድግስ፤

ሁለቱም መንግሥቶች ያዘጋጁት ድግስ የመሰነባበቻቸውና የፍፃሚያቸው ምልክትና ዋዜማ ሆኖ ተከሰተ!

ወያኔም ቢሆን ከፊቱ ለነበሩት ሁለት መንግሥቶች የታያቸው ታይቶት ይሆናል!!
ከዚህ በፊትም ቢሆን ራሱ የወያኔ መሪ (መለስ ዜናዊ) "ጠንብተናል" ፤ " በስብሰናል" ብሎ በድርጅቱ ላይ መስክሮ እንደነበረ ማንም የማይረሳው ነው::

ስለሆነም ሚሊኒየሙን አስታክከው ወያኔዎች በሸተተውና በበሰበሰው ስርዓታቸው ላይ አደይ አበባ በመበተንና ርችት በመተኮስ ለመንፃትና ለመቆናጀት የሚያደርጉት የጣዕረ-ሞት/ የጉደንድ አፋፍ ጥረትና ትርኢት ይሆናል።
የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀሎት ግን የወያኔን ምኞት የሚቃረን ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚመኘውና የሚታገለው ወያኔን አሽቀንጥሮ ወደ ዘላለማዊ ቤቱ/ ወደ መቃብሩ ገፍትሮ ለመጣል ነው።

ወያኔ የነጠቀውን ነፃነቱንና መብቱን መልሶ ከእጁ ለማስገባት ነው።
ወያኔ "ወንድማችን" ነው። "አጋራችን ነው"። ተወያይተንና ተፈቃቅረን " ሥልጣን እንጋራለን"። "ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንመሰርታለን"። የሚሉ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶችና የወያኔ ወዳጆች (" ተቃዋሚ ወያኔዎች = ድብቅ ወያኔዎች") ናቸው!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት ይጠንክራል!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚያካሂደው ትግል ያሸንፋል!